# ትምህርት የማካታተል ደንቦች

## I. አላማ

እነዚህ ደንቦች በዝርዝር የሚገልፁት፤
- የአሌክሳንደሪያ ከተማየ ሕዝብት/ቤቶች ትምህርት የማካታተል ፖሊሲ፣
- የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዝኑ ለቁጥጥር የሚጠቀምባቸው ደንቦች እና ያለፍቃድ ሚርፈድ ምላሺ አሰጣጥ፣ እንዲሁም
- ያለምንምፈቃድ የሚርፈድ ባህሪ የሚያስከትለውሁኔታ።

## II. ትርጓሜዎች

A. **የትምህርት ማስጨቀናት** የሚያካትተውሙሉ ቀን እና /ወይምበሚደበኛነት ለአንድ ተማሪ በተዘጋጀ የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ ያለውየትምህርት ክፍል ጊዜ ነው።

B. **በፍቃድ መቅረት** ማለት በደንቡበዝርዝር በተቀመጠውመሰረት በወላጆች ለትምህርት ቤት አስተዳደሩ በቀረበ በአንድ ምክንያት አንድ የትምህርት ሙሉ ቀን አለመገኘት ነው። ከትምህርት ቤት ከመቅረት በፊት ወላጅ/ አሳዳጊ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ለምን እንደሚቀሩ ምክንያት ማሳወቅ አለባቸውወይምከቀሩ በኋላ ባሉት ከ3 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው።

C. **ያለፈቃድ መቅረት** ማለት (i) አንድ ተማሪ ለእርሱ/ለእርሷ የተዘጋጀለትን/ላትን ሙሉ የትምህርት ቀን አለማካታተል እና (ii) ተማሪው ከቀረበት ቀን በኋላ ባሉት ቀጣይ 3 ቀናት ውስጥ በቂ አሳማኝ ምክንያት ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛ አልቀረበም ወይምከዚህ ደንብ ውጭ ባለው ሁኔታ ምክንያት ቀሪ እንደሆነ በወላጅ/አሳዳጊ የቀረበ ምክንያት የለም። በወላጅ/አሳዳጊ ተቀባይነት ያለውአሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ያለፈቃድ መቅረት የሚለውን ወደ በፈቃድ መቅረት ሊቀይረውይችላል ።

D. **ያልተረጋገጠ መቅረት** ማለት በወላጅ/አሳዳጊ ምንም ዓይነት ሚረጃ ልውውጥ ያልተደረገበት ማለት ነው። ተማሪው ከቀረበበት ቀን በኋላ ባሉት 3 ቀናት ምንም ግንኙነት ከሌለ ያልተረጋገጠ መቅረት ወደ ያለፈቃድ መቅረት ሊቀየር ይችላል።

E. **የተረጋገጠ መቅረት** ማለት ወላጅ/አሳዳጊ ከትምህርት ቤት ጋር ግንኙነት በማድረግ ስለመቅረቱ ምክንያት ያሳወቁበት ሁኔታ ማለት ነው።

F. **ተደጋጋሚ መቅረት** ማለት በፍቃድ/ያለፈቃድ መቅረት በማንኛውም ምክንያት በትምህርት ዓመት አሰር በመቶ ወይምከዚያ በላይ ለሚሆን ጊዜ መቅረት ድምር ማለት ነው።

G. **ያለምክንያት መቅረት (ትራወንሲ)** ማለት በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ከአምስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ያለፍቃድ ወይም ያልተረጋገጠ መቅረት ነው። በኮመንዌልዝ ቨርጂኒያ ያለምክንያት መቅረት (ትራወንሲ) ህግ እንደተደነገገው ማንናቸውምሁሉምልጆች በየቀኑ በትምህርት ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል።

H. **ሚርፈድ** የሚለው ቃል ትርጉሜየ ትምህርት ቀን ወይምአንድ የትምህርት ክፍል ከተጀመረ በኋላ መድረስን ያመለክታል።

I. **በትምህርት ላይ የማኘት ስብሰባ** በፊት ለፊት የሚደረግ ስብሰባ ወይም የማናኛ ቴክኒዎሎጂ ማሳሪያ በማጠቀም ግንኙነት ማድረግን ያማላክታል። <u>ከስድስት ጊዜ ያለፈቃድ መቅረት</u> በኋላ ስብሰባ ማካሄድ አለበት እና ስብሰባውቢያንስ የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ ፣ ወላጅ/ አሳዳጊ እና እንደአስፈላጊነቱ ተማሪውን ማካተት ይኖርበታል። ስብሰባው በተጨማሪ የትምህርት ቤት አማካሪ፣ የትምህርት ቤት የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ፣ የት/ቤት ሳይኮሎጅስት፣ የትምህርት ቤቱን ኢንተርቬንሽን ሰራተኛ እና እንደአስፈላጊነቱ የማህበረሰቡን ተወካይ ሊያካትት ይችላል ከትምህርት ቤት የመቅረት ችግሮችን መፍትሔለማግኘት እና አስፈላጊ ከሆነ አሁን በስራ የዋለውን ትምህርት የማከታተል እቅድ እንደገና ለማከለስ ።

J. **ትምህርት ማከታተል(አቴንዳንስ) እቅድ** የሚዘጋጀውየተማሪውን ትምህርት ያለማከታተል ችግር ለማስወገድ እና ተማሪውበመደበኛ የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ እንዲከታተል ለማድረግ በጋራ በትምህርት ቤቱ ተወካይ ማለትም በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይምተወካዩ እና በተማሪውነው። ተማሪውያለፈቃድ ከአምስት ጊዜ በላይ የቀረ ከሆነ ትምህርት የማከታተል (አቴንዳንስ) እቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል። መፍትሄ የሚፈለግ (ኢንተርቬንሽን) እና/ወይም ስብሰባዎች በተማሪው የሚደጃ ሲስተም ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል።

K. **ወደ ፍርድ ቤት ማላክ** ማለት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ቀጥታ ግንኙነት ከተደረገ በኋላ እና ተማሪውለሰባተኛ ጊዜ ያለፈቃድ ከቀረ በኋላ የአቤቱታ ማማልከቻ ለወጣቶች እና የቤት ውስጥ (ዶማስቲክ) ግንኙነቶች ፍርድ ቤት ማቅረብ ነው። ስለተማሪውያለፈቃድ መቅረት መፍትሔጣልቃ መግባት የተዘጋጀ እቅድ ፣ የስብሰባውውጤት የያዘ ሰነድ እና የቨርጂኒያ ህግ 22.1-258 በትክክል በስራ መዋሉን የሚያሳዮ ሚደጃዎች ለተቀባዮ የፍርድቤአት መዘጋቢ ሰራተኛ መቅረብ አለበት።

L. **ዘርፈ ብዙ ባለሞያ ቡድን** በትምህርት ቤት ላይ የተማሰረተ የተማሪውን ሰነዶች ፋይል ለመማላከት የሚሰበሰብ እና አስቀድሞ ጣልቃ በመግባት ስራ የሚሳተፍ እና ከማጠን በላይ የሆነውን የመቅረት ሁኔታ በተማላከተ በትምህርት ቤት ላይ የተማሰረተ ጉዳይ የማከታተል ስራ ጭምር በሚደረግ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል። እነዚህ አገልግሎቶች የአካዳሚ፣ የማህበራዊ፣ የስሜት እና የቤተሰብ ጉዳዮችን መፍትሄ በሚፈለግ መደበኛ የትምህርት ማከታተል የማሻሻል ስራ ያከናውናሉ። የቡድን አባላት በእነዚህ የሚወሰን ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፤ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ፣ የትምህርት ቤት የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ፣ የት/ቤት ሳይኮሎጅስት፣ የትምህርት ቤቱ የልዮ ትምህርት አስተማሪ፣ የጠቅላላ ትምህርት አስተማሪ ፣ የትምህርት አቴንዳንስ ክትትል ኋላፊን ሊያካትት ይችላል። የኮሚዩኒቲ ተወካዩምእንደአስፈላጊነቱ ሊገኝ ይችላል።

M. **ወላጅ/ አሳዳጊ፤** ማለት ወላጅ/ጆች ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ(ዎች) ፤ ህጋዊ ጠበቂ(ዎች)ወይምሌላ ሰው(ዎች) ሕጋዊ የመቆጣጣር ወይምኋላፊነት ያላቸውናቸው።

N. **ርእሰ መምህር ወይምተወካይ፤** ማለት የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይምበደንቡ ማሳረት ማሳፈርቱን የሚያሟላ በርእሰ መምህሩ የተወከለ ሌላ አስተዳደሪ ወይምሌላ የትምህርት ቤቱ ኋላፊ ማለት ነው።

## <u>III በትምህርት ማኘት የሚያሳይ (አቴንዳንስ) ኮድ አሰጣጥ</u>

የአሌክሳንደሪያ ከተማየሕዝብት/ቤቶች የቨርጅኒያ ኮመንዌልዝ የግዴታ ትምህርት ማካታተል (አቴንዳንስ) ህግ (22.1-258) እና የቨርጂኒያ የአስተዳደር ህግ(8VAC20-730-10) በትክክል በማካተል ትምህርት የማካታተል (አቴንዳንስ) መሚያ ያዘጋጃል እንዲሁም በስራ እንዲዉል ያደርጋል። እኒዚህ ትምህርት የማካታተል(አቴንዳንስ) ደንቦች የJEA(በግዴታ ትምህርት የማካታተል ፖሊሲ) በስራ እንዲዉል ያደርጋሉ።

ካሉት ትምህርት የማካታተል(አቴንዳንስ) ኮዶች ማካከል አንደኛውእንደአግባብበቱ በእያንዳንዱተማሪ በየክፍል ጊዜው(ፔሬድ) በየትምህርት ቀኑ እንዲገባ ይደረጋል።

| **ኮዶች** | **የትምህርት ማካታተል ምድብ** | **ዝርዝር መግለጫ** | **ተጨማሪ ከግንዛቤየሚገቡጉዳዮች** |
|---|---|---|---|
| **ካልተቀየሩ በነባሪነት የሚያገለግሉ ኮዶች** | | | |
| ኮድ ማጠቀም ተፈላጊ አይደለ | በክፍል መገኘት | ትምህርት ማካታተል (አቴንዳ በአውቶማቲክ የሚያታይ ኮድ<br><br>ተማሪውበክፍል ውስጥአለ እ በሰዓቱ ተገኝቶል። | ይህ በነባራዊነት የሚሰጥኮድ ለእያንዳንዱተማሪ የሚሰጥ ነው። ተማሪውበክፍል ያልተገኘ ከሆነ አስተማሪ የተማሪውን ሪኮርድበፖወር-ቲቸር (Power-Teacher) መቀየር አለበት። አስተማሪው የተማሪዋችን በክፍል መኖር ስም የሚይጠራ (አቴንዳንስ) የሚይዝ ከሆነ ለዚያ ቀን ወይምለዚያ ክፍል የተማሪውን አቴንዳንስ "አለ-ፕረዘንት" የሚለውን ኮድ ይጠቀማል። |
| A | ያልተረጋገጠ | ለቀሪ የሚያገልግል ኮድ | አስተማሪውበክፍል ውስጥ ተማሪዋችን ስምበመጥራት (አቴንዳንስ) ከወሰደ በኋላ ተማሪውን አለመኖሩን ከታወቀ ይህን ኮድ ይጠቀማል። ይህም የሚያሳየውየትምህርት ቤት አስተዳደሩ ከቤተሰብ ወይምሌላ ኋላፊነት ካለውአካል ስለተማሪውመቅረት የደረሰው ሚረጃ ያለመኖሩን ነው። |
| **የመቅረት ኮዶች** | | | |
| D | ፍርድ ቤት/ ህግ | ይህ ኮድየሚያሳየውይፋ የሆነ የፍርድቤት /ህጋዊ | ይህ በጥቅምላይ የሚውለው ተማሪውበፍርድቤት የፍርድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሰነድ ወይም ከፍርድ ቤት ተወካይ በቃል የተገለፀ ሚረጋገጫ መድረሱን ነው። | ሂደት የተሳተፈ መሆኑንና ወይም ሌላ አስገዳጅነት ባለው ህጋዊ ተግባር በሚከሄድበት እንደነበረ የሚያሳይ ነው። |
| F | የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ | ይህ ኮድ የሚያሚላክተው የቅርብ ቤተሰብ የተረጋገጠ ሞት የጋጠመ መሆኑን ወይም የህክምና ድንገተኛ ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን ወይም ከአንድ ቦታ የሚናቀል ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑን ነው። | ወላጅ/ አሳዳጊ ለትምህርት ቤት ማሳወቅ እና ለመቅረቱ ሰነድ ማስረጃ መቅረብ አለበት። ይህን ኮድ ለቤተሰብ የእረፍት ጉዞ ምክንያት ለማስጠት ማ ልገል አይቻልም። |
| G | የሚረፊያ ቦታ ቆይታ | ይህ ኮድ በአገልግሎት የሚውለው ተማሪዋች በፍርድ ቤት ትእዛዝ ማሰረት በሚረፊያ ቦታ እያሉ ትምህርት ቀን እንዲከታተሉ ሲደረግ ነው። | |
| H | በቤት መቆየት | ይህ ኮድ በጥቅምላይ የሚውለው አንድ ተማሪ በቤት ውስጥ በሚቆይበት ወቅት በስቴቱ ህግ ማሰረት የህክምና የምስክር ወረቀት እንደቀረበ በቤት ውስጥ እያለ ትምህርት አገልግሎት እንዲያገኝ ፍቃድ ሲያገኝ ነው። በቤት ውስጥ ቆይታ የሚሰጥ ትምህርት በሚከተሉት ሁኔታዋች ሊሰጥ ይችላል፤<br>• የከፋ የአካል ወይም የአእምሮ ህመም<br>• በሆስፒታል መተኛት<br>• የወሊድ /የወላጅነት ፈቃድ<br>• የሚያባብሱ ከባድ ሁኔታዋች ሲኖሩ | የትምህርት ቤት አማካሪ እና በቤት ውስጥ ለሚቆዮ ተማሪዋች ጉዳይ አስተባባሪ ይህን ሂደት የሚያስተባብሩ ሲሆን የሚሰጠውን አገልግሎት የመጀመሪያ እና የሚጨረሻ ቀናትን ይወስናሉ። በቤት ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት በሚማለከት የሚሰጠው ውሳኔ ለትምህርት ቤቱ ሪጅስትራር እና ለትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪቡድን አባለት እንዲያውቁት ይደረጋል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| I | ህመም | ወላጅ/ አሳዳጊ ስለተማሪው ሚታመምሚረጋገጫ<br>(የ ቃል/የ ፅሁፍ) ማስጠት<br>አለባቸው፡፡<br><br>ይህ ኮድ በተጨማሪ<br>የ ሚያገ ለግለውተማሪው ቀሪ የ ሆነ በት ምክንያት<br>በአካል ወይምበአእምሮ ጤንነ ት ችግር ምክንያት<br>መሆኑን በህክምና ባለሞያ የ ተሰጠወረቀት ሲቀርብ<br>ነ ው፡፡ | በህመምምክንያት አንድ ተማሪ ትምህርት ማካታተል ሲያቅተው<br>አሳዳጊ ውወይምሀኪሙ<br>ከትምህርት ቤት ከመቅረቱ በፊት<br>ወይምከቀረበት ጊዜ በኋላ ባሉት<br>3 ቀናት ውስጥየ ፅሁፍ ሚረጋገጫ<br>መቅረብ ይኖርበታል።<br><br>**የ ጠነ ከረ /የ ተራዘ መሕመም**<br>ተማሪዋች በከፋ ህመምወይም<br>በአካል ጉዳት ምክንያት ለረዥም<br>ጊዜ ቀሪ ከሆኑ ከሀኪምይፋ<br>ማስረጃ ለትምህርት ቤቱ መቅረብ<br>ይኖርበታል።<br><br>ህመሙበተደጋገ ሚወይምለብዙ<br>ጊዜ የ ሚከሰት ከሆነ ከትምህርት<br>ቤቱ ነ ርስ፣ አስተዳደሪ እና<br>አግባብነ ት ካላቸውየ ድጋፍ ሰጪ<br>ቡድን አባላት ጋር በመማከር<br>ተገ ቢውን የ ድጋፍ አገ ልግሎት<br>የ ጤና እንክብካቤ እቅድ ጭምር<br>በስራ እንዲውል ሚድረግ ተገ ቢ<br>ይሆና ል። |
| P | በትምህርት ቤት ውስጥእገ ዳ | ይህ ኮድ በጥቅምላይ<br>የ ሚውለው የ ትምህርት ቤት<br>አስተዳደሩ ተማሪውን<br>በትምህርት ቤት ውስጥ<br>እገ ዳ (ISS) ወይምአማራጭ<br>የ ማስተማር ድጋፍ (AIS)<br>ማእከል በመመደቡ<br>ምክንያት አንድ ተማሪ<br>ከክፍል ሲቀር ነ ው፡፡ | ወላጅ/ አሳዳጊ እገ ዳው<br>የ ሚጀመርበትና የ ሚያበቃበት<br>ቀን እንዲያውቁት ይደረጋል።<br>ተማሪውበአስተዳዳሩ<br>በተገ ለፀውቀን ወደ ሚደበኛ<br>ክፍሉ መመለስ ይኖርበታል። |
| R | ሐይማኖት | ይህ ኮድ በተማሪው<br>በሚያምንበት እምነ ት<br>አሰራር ወይምየ ሀይማኖት<br>ባህል ማክበር ከትምህርት<br>መቅረት ያመለክታል። | ተማሪዋቹ ከሚከተሉት እምነ ት<br>ወይምየ ሃይማኖት ባህል ጋር<br>በተያያዘ ከክፍል በፈቃድ<br>መቅረታቸውን ያመለክታል። |
| U | ያለፈቃድ | ያለፈቃድ መቅረት<br>የ ሚከተሉትን ሁኔ ታዎችን<br>ያካትታል አንድ ተማሪ<br>ያለፈቃድ ወይምያለምንም<br>ማስረጃ በአንድ<br>የ ትምህርት ክፍል ወይም<br>ትምህርት በሚሰጥበት ቀን<br>አለማ ኘትን ያካትታል። | ያለፈቃድ መቅረት የ ሚከተሉትን<br>ሁኔ ታዎችን ያካትታል አንድ<br>ተማሪ ያለፈቃድ ወይምያለምንም<br>ማስረጃ በአንድየ ትምህርት<br>ክፍል ወይምትምህርት<br>በሚሰጥበት ማት ቀን<br>አለማ ኘትን ያካትታል። እና<br>የ ትምህርት ቤት ሰራተኞችም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ለምሳሌ የቤተሰብ ጉዞ ፣ ያለስራ ማዞር፣ አውቶብስ ማምለጥ ወይም በእንቅልፍ ምክንያት መቅረት<br><br>በትምህርት ዓመት ጊዜ የቤተሰብ የእረፍት ጉዞ ያለፍቃድ መቅረት በሚል ይመዘገባል። | ተማሪው ከቀረበት 3 ቀናት ውስጥ ምንም ሚረጃ አልደረሳቸውም። ይህ በተጨማሪ የሚያካታታቸው ወላጅ/ አሳዳጊ ለመቅረቱ በዚህ ደንብ ያልተገለፀ ምክንያት የሰጡ መሆኑን ነው። በወላጅ/አሳዳጊ ተቀባይነት ያለው አሳማኝ ምክንያት ሲቀርብ የትምህርት ቤት አስተዳደሩ በቨርጂኒያ የትምህርት ማካታተል ኮድ አሰጣጥ ማስረት ያለፈቃድ መቅረት የሚለውን በፈቃድ መቅረት ወደሚለው ሊቀይረው ይችላል ። |
| V | የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ | የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች የሚያካትተው በፍቃድ እና በቅድሚያ የተረጋገጠ መቅረት ከትምህርት ቤት የስፖርት እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዘ ፣ የሜዚቃ ሚርሽ፣ ROTC፣ የዘማሪ ባንድ ወይም ሌላ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኛ ኋላፊነት የሚካሄድ የአካዳሚክ ለብ። ይህ ኮድ በተጨማሪ በትምህርት ቀን ተማሪው ከትምህርት ቤት ኋላፊዎች እና ሌላ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በሚደረግ ስብሰባ ምክንያት በፍቃድ መቅረት ያካትታል። | የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ አስተባባሪዎች ወይም የዲፖርትሜንት ሚሪዎች በሚረጋገጥ እንቅስቃሴ ከሚኪያሄዱ በፊት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ከተደረገ በኋላ ወዲያውኑ ለተሚደቡት አስተማሪዎችና የተማሪዎችን በክፍል መገኘት ለሚከታተሉ ሰራተኞች ያሳውቃሉ ። |
| S | እገዳ (ከትምህርት ቤት ውጭ) | ይህ ኮድ በጥቅምላይ የሚውለው የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ተማሪውን በትምህርት ቤት ውጭ እገዳ በሚወሰኑ ምክንያት አንድ ተማሪ ከክፍል ሲቀር ነው። | ወላጅ/ አሳዳጊ እገዳው የሚጀሚርበትና የሚያበቃበት ቀን እንዲያውቁት ይደረጋል። ተማሪው በአስተዳዳሩ በተገለፀው ቀን ወደ ሚደበኛ ክፍሉ መመለስ ይኖርበታል። |
| **የሚርፈድ ኮዶች** | | | |
| T | ሚርፈድ | ሚርፈድ የሚያካትተው ማንኛውንም ያለፈቃድ ወይም ያልተረጋገጠ ከክፍል ሚርፈድ ነው። | ይህ ኮድ ተማሪው ከክፍል ዘግይቶ የደረሰ መሆኑን ያለበቂ ምክንያት ወይም ሳይረጋገጥ የዘገየ መሆኑን በሚደበኛነት በአስተማሪ የሚጠቀምበት ኮድ |

ቪ.ዲ.ኦ.ኢ ያለፈቃድ መቅረትን የሚመለከቱን ሚረጃዋችን በሚከተለውየጊዜ ልዩነት ያሰባስባል፤

ፎል ሴሚስተር፤ ኦክቶበር 1
ስፕሪንግ ሴሚስተር፤ ሚርች 31
የትምህርት ዓመት ሚጨረሻ፤ ጁን 30
ሰመር ሴሚስተር፤ ኦገስት 30

የቨርጂኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት የተጠያቂነት እርምጃዋች በትምህርት ቤቶች አስተዳደር ዲቪዝኖችን የኤሌክትሮኒክስ የትምህርት ቤት ማገኘት(አቴንዳንስ) የመፍትሄ ጣልቃ መግባት እርምጃዋች የሚመለከቱ የሚረጃ አያያዝ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ በሦስት የተወሰኑ ማከኮች ላይ ያተኩራል፤

- በትምህርት የማገኘት (አቴንዳንስ) እቅድ ኮድ ሚረጃ አያያዝ።
  ይህ ክፍል ሚሟላት ይኖርበታል ያለፈቃድ መቅረት 5ኛ ላይ ሲደርስ።
- በትምህርት የማገኘት (አቴንዳንስ) ስብሰባ ኮድ ሚረጃ አያያዝ
  ይህ ክፍል ሚሟላት ይኖርበታል ያለፈቃድ መቅረት 6ኛ ላይ ሲደርስ።
- ወደ ፍርድ ቤት የማላክ /አቤቱታ ሂደት ኮድ ሚረጃ አያያዝ
  ይህ ክፍል ሚሟላት ይኖርበታል ያለፈቃድ መቅረት 7ኛውላይ ሲደርስ።

2. <u>አስር ቀን “አለማገኘት” አሰራሮች የሚመለከት ሚረጃ አያያዝ በሴፕቴምባር</u>
   የቨርጂኒያ የአስተዳደር ህግ (8VAC20-730-30) የተገለፀው፤

   “የሚረጃ አሰባሰብ ተማሪውትምህርት በሚጀምርበት በትምህርት ዓመት የመጀመሪያ ቀን መጀመር አለበት። በቨርጂኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት በተዘጋጀውአሰራር ማስረት እያንዳንዱ የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዥን በእያንዳንዱ ተማሪ አቴንዳንስ ደረጃ ያለፈቃድ መቅረት ብዛት ጭምር የሚያሳይ ሪፖርት ማዘጋጀት ይኖርበታል። የተማሪው አቴንዳንስ ሚረጃ የሚጠራቀም ሲሆን ሚረጃ ማያዝ የመጀምሪውየትምህርት ዓመት የመጀመሪያውቀን ወይምተማሪውበይፋ በትምህርት ቤቱ ተመዝግቦ በሚጀምርበት ቀን ነው። ሁሉምበትምህርት አለማገኘት ቀናት ሚረጃ የሚጠራቀምሲሆን ይህምበመጀመሪያውመቅረት ይጀምራል። ይህን ሚረጃ ለማሰባሰብ ሲባል ያለበቂ ምክንያት መቅረት የሚጀምሪውበመጀመሪያውያለፈቃድ መቅረት ሲሆን እና ይህምየሚጠራቀምይሆናል።

   ሁሉም በይፋ ለመማር የተመዘገቡ ተማሪዋች እና በትምህርት ቤት ሪከርድ በተማሪነት የሚታወቁ በትምህርት ባለማገኘት እንደቀሪ መመዝገብ አለባቸው ሁኔታውን የሚቀይር ተቀባይነት ያለውሚረጋገጫእስከሚቀርብ ድረስ። በተራዘመ የእረፍት ጉዞ ምክንያት በትምህርት ላይ የማይገኙ ተማሪዋች ፣ የውጭአገር ጉዞ እና ሌሎች እንደ “ያለፍቃድ መቅረት” የሚቆጠሩ ጉዳዮች በዚያውሚልክ መመዝገብ አለባቸው።

B. **ሙሉ ቀን መቅረት ትርጎሜ**
   በቨርጂኒያ የአስተዳደር ህግ ማስረት ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በሁለተኛ ደረጃ ላሉት አንድ ተማሪን ሙሉ ቀን መቅረት በሚል የሚመዘግበው በአንድ የትምህርት ቀን የሚሰጠውን በሁሉምየትምህርት ክፍሎች ሳይገኝ ሲቀር ነው።

C. **በፈቃድ መቅረት**

1. በቨርጂኒያ የአስተዳደር ህግ ማስረት (8VAC20-730-10) የተማሪ መቅረት በፍቃድ እንደቀረ ሊታይ ይችላል ከወላጅ/አሳዳጊ እና /ወይም ከሌላ ባለሞያ የሚቀርበው ሚረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ። በፍቃድ መቅረት ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታል ሆኖምግን በእነ ዚህ ብቻ አይወሰንም፤
   a. የህመምሕክምና (የአካል ወይምየአእምሮ) አንድ ተማሪ 3 ተከታታይ ቀናት ወይም በአንድ የትምህርት ዓመት 10 ወይምከዚያ በላይ ቀናት ከቀረ ከዶክተር ማስረጃ ማቅረብእንዲሚኖርበት ርእሰ መምህሩ ማጠየቅ አለበት።
   b. የህክምና የጥርስ ምርመራዎች
   c. የሃይማኖት ቀናት በአል ማክበር
   d. የተማሪ የፍርድቤት ቀጠሮ
   e. በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸው ተማሪዎች (በትምህርት ቤት ውስጥእና ከትምህርት ቤት ውጪ)።
   f. ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ (ISS) ፣ በአማራጭየትምህርት ድጋፍ (AIS) ማእከል ወይምከትምህርት ቤት ውጭእገዳ (OSS)።
   g. የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎች (የቅርብ ቤተሰብ ማጣት፣ ያልታሰብየመኖሪያ ቤት ማልቀቅ፣ የቤተሰብ አባል ከፍተኛ ጉዳት ማካሰት) ወላጅ/ አሳዳጊ የረዥምጉዞ ወይምየእረፍት ጊዜ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የእረፍት ጊዜ እና የበዓላት ጊዚያት ጋር በሚስማማሁኔታ ማቀድ ይኖርባቸዋል።
   h. የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትራንስፖርት አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ሚርፈድ

2. <u>አስቀድሞበተሰጠፈቃድ መቅረት</u>
   አስቀድሞ የሚሰጥ ፍቃድ ማጠየቂያ ቅፅ በተወሰኑ ሁኔታዎች ሊቀርብ ይችላል። የሚከተሉት አስቀድሞ በተሰጠ ፍቃድ ማስረት ከትምህርት የመቅረት ሁኔታዎችን ምሳሌዎችን ያካትታል (ከማስረጃዎች ጋር)፤
   a. የዩ.ኤስ ሚሊተሪ ወይም የጦር ኋይል በግዳጅ ላይ ያሉ አባላት ቤተሰቦች ጉብኝት።
   b. በእስር ላይ ያሉ የቤተሰብሃላፊዎች ጉብኝት፣
   c. ከወታደራዊ ሜልሚዮች ጋር የተያዘ ቀጠሮ፣
   d. ከዮኒቨርስቲ/ኮሌጅ ምልመላ ዲፖርትሜንት ጋር የተያዘ ቀጠሮ፣
   e. ወላጅ/ አሳዳጊ ከስራ ጋር በተያያዘ በጉዞ ላይ ባሉበት ወቅት የትምህርት ቤት ተማሪዎች እድሜያቸው 12 ወይም ከዚያ በታች የሆነ በቤት ውስጥ ብቻቸውን /ያለጠበቂ መተውየማይቻል ።

አስቀድሞየሚሰጥ ፍቃድ ማጠየቂያ ቅፃች ለመቅረት ከታሰበበት ቀን ቢያንስ 5 ቀናት በፊት መቅረብ ይኖርባቸዋል እንዲሁምአስቀድሞየሚሰጥ ፍቃድ በቅድሚያ በትምህርት ቤት አስተዳደር ፈቃድ ማስጠት ይኖርበታል። እላይ በተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች የተማሪውተሳትፎ ከተከናወነ 3ቀናት በኋላ መቅረብ ማስረጃዎች መቅረብ ይኖርበታል።

3. <u>የህመምሕክምና (የአካል ወይምየአእምሮ)</u>
   a. ወላጅ/ አሳዳጊ በቅድሚያ ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛ የተማሪውን ማታመም በቃል ወይምበፅሁፍ ያሳውቃል። ተማሪው በአንድ የትምህርት ዓመት 10 ወይምከዚያ በላይ መቅረት ሪከርድ ካለውርእሰ መምህሩ ከሃኪምማስረጃ እንዲቀርብ ማጠየቅ ይኖርበታል። በህመም ምክንያት አንድ ተማሪ ትምህርት ማከታተል ሲያቅተው

አሳዳጊው ወይም ሀኪሙ ከትምህርት ቤት ከመቅረቱ በፊት ወይም ከቀረበት ጊዜ በኋላ ባሉት 3 ቀናት ውስጥ የፅሁፍ ሚጋገ ጫመቅረብ ይኖርበታል።

b. በተደጋጋሚ ወይም በተከታታይ ህመም ሲያጋጥም የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ቡድን አባላት ተገቢ የሆነ የጤልቃ መግባት ድጋፍ የተማሪው የጤና አጠባበቅ እቅድ የሚጨምር ሊያዘጋጁ ይችላሉ። በአንድ የትምህርት ዓመት ከ10 የህመም ቀናት በላይ ሲያጋጥም የጤና አጠባበቅ እቅድ ማታየት ይኖርበታል።

c. አንድ ተማሪ በህመም ምክንያት ከ3 ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ቀናት ሲቀር ከሃኪም ይፋ የሆነ ማስረጃ ይህንኑ ጉዳይ እንዲከታተል ለተመደበ የአስተዳደር ረዳት ሰራተኛ ማቅረብ ይኖርበታል። ከ3 የትምህርት ቀናት በኋላ የሃኪም ወረቀት ካልቀረበ ያለፈቃድ መቅረት በሚል ሊቀየር ይችላል።

D. **ያለፈቃድ መቅረት**

በቨርጂኒያ የአስተዳደር ኮድ (8VAC20-730-10) ማስረት (i) አንድ ተማሪ ለእርሱ/ለእርሷ የተዘጋጀለትን/ላትን ሙሉ የትምህርት ቀን ካልተከታተለ/ች እና (ii) ተማሪው/ዋ ከቀረበት/ችበት ቀን በኋላ ባሉት ቀጣይ 3 ቀናት ውስጥ በቂ አሳማኝ ምክንያት ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ካልቀረበ ወይም ከዚህ ደንብ ውጭ ባለው ሁኔታ ምክንያት ቀሪ እንደሆነ /ች በወላጅ/አሳዳጊ የቀረበ ምክንያት ከሌለ ያለፈቃድ መቅረት እንደተፈጠረ ይቆጠራል። <u>አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ አምስት ወይም ከዚያ ቀናት በላይ ያለፈቃድ ከቀረ ያለበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት እንደቀረ ይቆጠራል።</u>

1. **ያለበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት የሚያስከትለው ውጤት**
   a. <u>በተማሪው ላይ የሚከተሉ ሁኔታዎች፤</u>
      i. አስፈላጊ የሆነ የትምህርት ጊዜ ማጣት
      ii. ተማሪው በትምህርት ዝቅተኛ ውጤት ሊኖረው ይችላል።
      iii. ተማሪው የገለልተኝነት እና የመገጤል ስሜት ሊኖረው ይችላል።
      iv. ተማሪው በይፋ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል (ከ15 ተከታታይ ቀናት በኋላ)።
      v. የተማሪው ጉዳይ ለአሌክሳንደሪያ ፍርድ ቤት የተማሪዎች አቴንደንስ የሚመለከት ፓናል ሊመራ ይችላል።
      vi. በቨርጅኒያ ህግ § 16.1-228 ,§ 16.1-241.2, 16.1-278.5 እና 16.1-278.4 ማሰረት የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች በወጣቶችና የቤት ውስጥ ግንኙነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸውልጆች (CHINS) ፋይል እንዲከፈት ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህም የሚከተለውን ሁኔታ ያስከትላል፤
         - ተማሪዎች በወጣቶች የሚረሚያ ቁጥጥር እና ክትትል ስር እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል።
         - ተማሪዎች በኮሚኒቲ አገልግሎት እንዲሳተፉ በፍርድ ቤት ሊታዘዙ ይችላሉ።
         - ተማሪዎች በአእምሮ የጤና ህክምና እንዲታዩ በፍርድ ቤት ሊታዘዙ ይችላሉ።
         - ፍርድ ቤቱ በኖርዘርን ቨርጅኒያ የአሌክሳንደሪያ የማቆያ ፕሮግራም እንዲቆዮ ወይም በኖርዘርን ቨርጅኒያ የወጣቶች የሚረፊያ ቤት እንዲቆዮ ሊያዝ ይችላል።
         - ተማሪዎች ከቤተሰባቸው ውጭ በቅርብ ዘመድ ቤት ፣ በህጻናት ማስደጊያ ተቋም ፣ በግል ድርጅት ወይም ተቋም ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ሰጪተቋምስር እንዲቆይ ሊወሰን ይችላል።

- ፍርድ ቤቱ የተማሪውን የመንጃ ፈቃድ ለማገድ ወይም እንዲሰረዝ ሊያደርግ ይችላል።

b. <u>በወላጅ/አሳዳጊ ላይ የሚከተሉ ሁኔታዎች፤</u>

i. ጉዳዩ ወደ አሌክሳንደሪያ ፍርድ ቤት የተማሪዎች አቴንደንስ የሚመለከት ፓናል ሊመራ ይችላል።

ii. በቨርጅኒያ ህግ §§ 22.1-262, 16.1-228 , 16.1-241.2, 16.1-278.5 እና 16.1-278.4 መሰረት የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች በወጣቶችና የቤት ውስጥ ግንኙነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት በወላጅ/ አሳዳጊ ላይ የአቤቱታ ፋይል እንዲከፈት ሊያደርጉ ይችላሉ። ይህም የሚከተለውን ሁኔታ ያስከትላል፤

- ወላጅ/ አሳዳጊ በአእምሮ የጤና ህክምና እንዲታዩ ሊታዘዙ ይችላሉ።
- ወላጅ/ አሳዳጊ ከፍተኛ የሆነ ቅጣት እንዲከፍሉ ሊታዘዙ ይችላሉ።
- ወላጅ/ አሳዳጊ የእስር ቅጣት እንዲቀበሉ ሊደርጉ ይችላሉ(የፍርድ ቤት ትእዛዝ በሚጥሱበት ወቅት)።
- ልጆቻቸውከወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲለዩ እንዲወጡሊደረግ ይችላል እና በቅርብ ዘመድ ቤት እንዲቆዮ ፣ በህጻናት ማሳደጊያ ተቆም፣ በግል ድርጅት ወይምተቆምወይምበማህበራዊ አገልግሎት ሰጪተቆም ስር እንዲቆይ ሊወሰን ይችላል።
- ከስራ በመቅረት የሚጠፋ ጊዜ / ሳይከፈል የሚቀር ደመወዝ

E. **አስቀድሞመልቀቅ**

በመደበኛ የትምህርት ሰዓት አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ግቢ በማንኛውም ምክንያት ሲወጣ ወላጅ/ አሳዳጊ በቅድሚያ ማሳወቅ አለባቸው እና በፅሁፍ ፈቃድ ማስጠት አለባቸው፡፡ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ የሆነ ወላጅ/ አሳዳጊ በትምህርት ቤቱ የመውጫያ መዝገብ ላይ ሚፈረምያስፈልጋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከትምህርት አስቀድሞለመውጣት በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች አቴንዳንስ ቢሮ በኩል ፍቃድ ማግኘት አለባቸውእና ለመውጣት የተዘጋጀውን አሰራር ማከተል ይኖርባቻዋል።

ርእሰ መምህሩ ተማሪውን ልጁን ኋላፊነት መውሰድ ለማይችል ስልጣን ለሌለውለማንኛውም ሰው መልቀቅ አይኖርበትም፡ ሁሉም ተማሪዎች እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ በአዋቂነት ለተመደቡ ተማሪዎች ጭምር እንዴት ከትምህርት ቤት መውጣት እንዲሚቻል የተቀመጠውን አሰራር ማከተል ይኖርባቸዋል። አስቀድሞ መውጣት መረጃ መዝገብ ይዘጋጃል። የትምህርት ቤት ሰራተኛ ከትምህርት አስቀድሞመውጣት የተለመደ መሆኑን ከተመለከተ ስለጉዳዩ ጥልቃ መግባት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

F. **ማርፈድ**

ማንኛውም ተማሪ የትምህርት ክፍል ወይም የትምህርት ቀኑ በይፋ ከተጀመረ በኋላ መድረስ እንደ ዘገየ ያስቆጥራል። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ዘግይተው ከደረሱ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተዘጋጀውን የምዝገባ ስርዓት ተከትለው መፈፀም ይኖርበታል። በተማሪውሪከርድ ውስጥ ተማሪውን የዘገየባቸው መረጃዎች እንዲቀመጥ ይደረጋል። በቨርጂኒያ የግዴታ ትምህርት ማከታተል ህግ ላይ በጣም የተደጋገመ ከትምህርት ቤት ማርፈድ ማርፈድ በተመለከተ በግልፅ የተቀመጠ ነገር ባይኖርም የተማሪዎችን አጠቃላይ የአካዳሚልምድ እና በተማሪው ውጤታማነት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ጉዳይ ነው፡፡ ማርፈድ በርእሰ መምህሩ የክፍል ወይም የትምህርት ቀን መጀመሪያነት በተወሰነ የትምህርት መጀመሪያ ሰዓት ያለፈ የተለያየ የጊዜ ማጠን የየዘ

ነው። ወላጅ/አሳዳጊ ተማሪው ከማቢያ ሰዓት በዘገየ በእያንዳንዱ ጊዜ የተማሪው አቴንደንስ እንዲከታተል ለተመደበ ሰራተኛ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስታወቂያ ማቅረብ ይኖርበታል።

**በፍቃድ ማርፈድ** ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታል ሆኖምግን በእነ ዚህ ብቻ አይወሰንም፤

1. የህክምና የጥርስ ምርመራዎች
2. የተማሪ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎች
3. በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸው ተማሪዎች (በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከትምህርት ቤት ውጪ)።
4. ከባድ እና ባልተጠበቀ ሁኔታ የሚያጋጥም የቤተሰብ ድንገተኛ አደጋ (የቅርብ ቤተሰብ ሞት፣ ያልተጠበቀ ከቤት ሚናቃል ፣ በቤተሰብ አባል የደረሰ ከባድ አደጋ፣ ወዘተ...) ወላጅ/ አሳዳጊ የረዥም ጉዞ ወይም የእረፍት ጊዜ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የእረፍት ጊዜ እና የበዓላት ጊዚያት ጋር በሚስማማ ሁኔታ ማቀድ ይኖርባቸዋል።
5. የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትራንስፖርት አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ማርፈድ

በትምህርት ቀናት ወደ ክፍል ማርፈድ በርእሰ መምህሩ ወይም በተወካዮ እንደሁኔታው እየታየ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል። በተማሪዎች ከማጠን በላይ የሆነ ያልተፈቀደ ወይም ያልተረጋገጠ ማርፈድ ሲጠራቅም የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ሰራተኛ፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና ከትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ቡድን አባላት ጋር በመሆን በተቻለ ፍጥነ ት ይህን ችግር ለማቃለል እቅድ ማውጣት ይኖርባቸዋል።

G. **አስራ አምስት ቀናት ተከታታይ መቅረት**

የግዴታ ትምህርት ማከታተል በሚደነግገው የቨርጅኒያ ህግ 22.1-254 ማስረት ማንኛውም አስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ከትምህርት ቤት የቀረ ተማሪ (ያለፍቃድ) በይፋ ከትምህርት ቤት እንዲሰረዝ ይደረጋል። እንደዚህ ያለ ሁኔታ ሲከሰት ርእሰ መምህሩ ወይምተወካዩ ተማሪውከትምህርት ቤቱ በሚሰረዝበት ወቅት ወላጆች በፅሁፍ እንዲያውቁ ያደረጋል። በቨርጅኒያ ህግ 22.1-254 ማስረት የ15 ተከታታይ ቀናት በመቅረት ምክንያት ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እንዲወጡ የተደረጉ ተማሪዎች ሌላ ትምህርት በየቀኑ እንዲከታተሉ ህጉ ያስገድዳል እና ይህን ህግ በሚተላለፍ እርምጃ እንዲወሰድ የሚቻልበት ሁኔታ ሊያፈጠር ይችላል። የ15 ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ ቀናት በመቅረት ምክንያት ተማሪዎች ከትምህርት ቤት እንዲወጡከተደረገ የሚከተሉት የጣልቃ መግባት ስራዎች ማከናወናቸውን ለሚያጋገጥ የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው።

1. የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪሰራተኞች ከተማሪውእና ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ግንኙነ ት ማድረግ አለባቸውወጣቱን የት እንደሆነ ለሚያጋገጥ።
2. የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የተማሪው የትምህርት እቅድ ማዘጋጀቱን ሚያጋገጥ አለባቸው።
3. የትምህርት ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ከአሌክሳንደሪያ ፍርድ ቤት አገልግሎቶች ሰራተኞች ጋር ጣልቃ መግባትን እና የውሳኔ አፈፃፀም በተማከለ ትብብር ማድረግ አለባቸው።

H. **የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎች**

ከባድ የሆነ የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ፈቃድ ይሰጣቸዋል። የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ ምሳሌዎች የሚያካትታቸው የሚከተሉትን ይጨምራል ሆኖምግን በእነርሱ አይገደብም፤

1. የቅርብ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል ሞት፤
2. የማይቀር ወይም ድንገተኛ የመኖሪያ ቤት ማጣት እና የቤተሰብ መፈናቀል/መልቀቅ
3. የቅርብ ቤተሰብ አባል የከፋ የጤና ችግር ወይም
4. ሌሎች

በቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት የተደጋገመ ወይም የተራዘመ መቅረት (ከሁለት ጊዜ በላይ) መቅረቱ ከተፈጠረ በኋላ ባሉት 3 ቀናት ውስጥ ተጨማሪ ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል። በተጨማሪም የቀርብ ስነስርዓት ለማካታተል 3 ወይም ከዚያ በላይ ተከታታይ የትምህርት ቀናት የቀሩ ተማሪዎች የቀብር ስርዓቱን የሚያሳይ ማስረጃ (ለምሳሌ፣ የቀብር ስርዓት ፕሮግራም፣ ወዘተ...) ተማሪው ከትምህርት ከቀረበት ቀን ባሉት 3 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ የቤተሰብ የእረፍት ጉዞን አይጨምርም፣ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን፣ ከኤሲፒኤስ ውጬ የተዘጋጀ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ወይም ከወላጅ/አሳዳጊ ቀጠሮ ጋር አብሮ መሄድን አያካትትም። ከዚህ በተለየ ሁኔታ የሚታየው በግዳጅ ላይ ያሉ የጦር ኋይል አባላት ቤተሰቦች ጉብኝት ወይም በእስር ላይ ያሉ የቤተሰብ ሃላፊዎች ጉብኝት ይጨምራል።

## I. የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች

የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች የሚያካትተው በፍቃድ እና በቅድሚያ የተረጋገጠ ከትምህርት ቤት የስፖርት ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴዎች፣ የሙዚቃ ሚርሽ፣ ROTC፣ የዘማሪ ባንድ ወይም በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኛ ኋላፊነት የሚከሄድ ሌላ የአካዳሚክለብ። የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ አስተባባሪዎች ወይም የዲፖርትሜንት ሚዎች በሚጋገጥ እንቅስቃሴ ከሚካያሄዱ በፊት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ከተደረገ በኋላ ወዲያውኑ ለተመደቡት አስተማሪዎችና የተማሪዎችን በክፍል ማገኘት ለሚከታተሉ ሰራተኞች ያሳውቃሉ ። በተጨማሪ ምሳሌዎች ፈቃድ የተሰጣቸው የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች የሚያካትቱት (ከሰነድ ማስረጃ ጋር)።

1. በትምህርት ቤት ውስጥ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኛ ጋር የሚደረጉ ስብሰባዎች (ከሰነድ ማስረጃ ጋር)።
2. ከወታደራዊ መልማዮች ጋር የተያዘ ቀጠሮ (ከሰነድ ማስረጃ ጋር)።
3. ከዮኒቨርስቲ/ኮሌጅ ምልመላ ዲፖርትሜንት ጋር የተያዘ ቀጠሮ (ከሰነድ ማስረጃ ጋር)።

## J. የቤተሰብ ጉዞ

ወላጅ/ አሳዳጊ የረዥም ጉዞ ወይም የእረፍት ጊዜ ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የእረፍት ጊዜ እና የበዓላት ጊዚያት ጋር በሚስማማ ሁኔታ ማቀድ ይኖርባቸዋል። የቤተሰብ ጉዞ ወይም የእረፍት ጊዜ ምክንያት ከትምህርት የቀሩ ተማሪዎች “ያለፍቃድ መቅረት” እንደሆነ ይመዘገባል ምንምእንኳን አስቀድሞ የተዘጋጀ ቢሆንም።

## K. የትምህርት ቤት ዝውውር

በዝውውር ምክንያት በአንድ ትምህርት ቤት የተመደቡ ሁሉምተማሪዎች (በአስተዳደራዊ ፕሮግራም ዝውውር፣ የወንድምእ/እህት መኖር ምክንያት ፣ ፎሪ ያልሆነ ሰራተኛ ተማሪ ) የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የትምህርት ማካታተል ቀሪ መሆን የሚምላከቱ በትምህርት ቤት በሰዓቱ ማ ኘትን የሚምላከቱ ደንቦችን ማካተል ይኖርባቸዋል ።

L. **የማጠለያ መኗሪያ እጦት**

የማጠለያ መኗሪያ እጦት ያለባቸውተማሪዎች ወይምለረዥምጊዜ በመኖሪያ ቤት ችግር ውስጥ ያሉ ከግዴታ ትምህርት ማካታተል እንዲቀሩ ፈቃድ አይሰጥም፡ ከተመደበላቸው የማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኞች ወይም ከትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዝኑ የማጠለያ መኗሪያ እጦት ያለባቸውአገናኝ ሰራተኛ ጋር አብሮ በማስራት ቋሚየሆነ ማጠለያ እና ማሳረታዊ የቤተሰብ ፍላጎት የሚምላበትን ሁኔታ በማካታተል ተማሪዎች ትምህርታቸውን ማካታተል ይጠበቅባቸዋል።

የፀደቀው፤ ጁላይ 6፣ 2018
የተሻሻለው፤ ሴፕቴምበር 7፣ 2018

የሕግ ማጣቀሻ፤ የቨርጂኒያ ሕግ፣ §§16.1-241.2, 16.1-254, 22.1-254, 22.1-258, 22.1-259, 22.1- 262, 22.1-265.

8 VAC 20-110-100.
8 VAC 20-730-10.
8 VAC 20-730-30.

የቃላት መፍቻ፤ JEA የግዴታ ትምህርት ማካታተል